አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

# አፍሪካ አካዳሚ

**AFRICA ACADEMY**

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት

በቴሌግራም

2

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

www.AfricaAcademy.com

## ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
## “ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”




“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”

**ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ**
**የአፍሪካ አካዳሚ**
**የርቀት ትምህርት**
**1441 ሒጅሪያ/2020**

- **አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ ትልቁ ወንጀል ምንድነው?**
  አላህ (ሱወ) ዘንድ ትልቁ ወንጀል በአላህ (ሱወ) ማጋራት ነው፡፡ አላህ (ሱወ) በቁርአን እንዲህ አለ (ማጋራት በርግጥ ታላቅ በደል ነው)
  ነቢዩ ሙሐመድም (ሰዐወ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (የወንጀሎች ሁሉ ትልቁ ወንጀል ምንድን ነው? ተብለው ሲጠየቁ (የፈጠረህ ሆኖ ሣለ በጌታህ አጋር ማድረግ ነው) ብለዋል፡፡

## የማጋራት አይነቶች ስንት ናቸው?

- **የማጋራት አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡**
- 1ኛው) **ትልቁ ማጋራት** ሲሆን እሱም ከኢስላም የሚያወጣና ቁርአን (አላህ በርሱ ማጋራትን ፈጽሞ አይምርም፡፡) ሲል የተናገረበት ነው፡፡ እሱም አራት ክፍሎች አሉት፡፡
- ሀ) የዱዓና የልመና ማጋራት/ሽርክ/ ልዒባዳ
- ለ) በኒያ፤ በሐሳብና በፍላጎት ማጋራት፤ለምሳሌ መልካም ሥራን ከአላህ ውጪ ለሆነ ለሌላ አካል መሥራት፤
- ሐ) የመታዘዝ ማጋራት ሺርክል ጧዓህ ምሣሌ አላህ ሐላል ያደረገውን ነገር ሐራም፤ ሐራም ያደረገውን ነገር ሐላል የሚያደርጉ ሰዎችን መታዘዝና አሚን ብሎ መቀበል ማለት ነው፡፡
- መ) የማፍቀር ማጋራት ሽርኩልሙሀበሩ ሲሆን እሱም አንድን ነገር እንደ አላህ (ሱ.ወ) አድርጎ መውደድ ነው፡፡
- 2ኛው) **ትንሹ ማጋራት** ሽርኩልአስገር ሲሆን ይህ አይነቱ ማጋራት የሰሪውን ሰው ከኢስላም አያወጣውም፡፡ ይህም ለሁለት የሚከፈል ሲሆን
- 1- ግልፅ የወጣ ለምሳሌ ከአላህ ውጪ በሌላ መማል፤ አንተና አላህ የሻው ይሆናል ወይም አንተና አላህ ባትኖሩልኝ ኖሮ እያሉ አላህን ከሰው እኩል ማድረግ አንዲሁም አላህን ዘንግቶ በሰበቦች ለምሳሌ በጦር መካላከያ ልብስ የሰው አይንን ፈርቶ አንገት ላይ በሚንጠለጠሉ ነገሮች፤ በገድና በአድባር በሌሎችም በነገሮች ሙሉ በሙሉ መተማመንን ይመስል ነው፡፡
- 2- ሌላው ድብቁ ማጋራት የሚባለው ሲሆን ለእዩልኝ ለስሙልኝ ብሎ ነገሮችን ማሰብ ማቀድና መስራት ነው፡፡

- **በትልቁ ማጋራትና በትንሹ ማጋራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**
- በመሀከላቸው ካሉ ልዩነቶች መካከል ትልቁን ማጋራት የፈፀመ ሰው በዚሁ በዱንያ እያለ ከኢስላም የወጣ መሆኑን ሲረጋገጥ፤ በአኺራም በገሀነምም ውስጥ እንደሚዘወትር ብይን ይሰጠዋል፡፡ ትንሹን ሽርክ የፈፀመ ሰው ከኢስላም እንደወጣ አይቆጠርም፡፡ በገሀነምም ውስጥ አይዘወትርም፡፡ ትልቁ ማጋራት መልካም ስራዎችን ሁሉ ሲያበላሽ፤ ትንሹ ግን ከሱ ጋር ግንኙነት ያለውን ስራ ብቻ ነው የሚያበላሸው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አለ፡፡ እሱም ትንሹ ሽርክ ሰውየው ንስሀ እስካልገባ ድረስ እንደትልቁ ሽርክ አይማርም? ወይንስ እሱም እንደሌሎቹ ታላላቅ ወንጀሎች በአላህ ፍቃድ ስር የሚጠቃለል ነው በሚለው ላይ የኡለማዎች የአቋም ልዩነት አለ፡፡ ይህም ጉዳዩ በጣም አስጊ ነውና ሰዎች አጥብቀው ሊርቁት ይገባል፡፡

- **ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለሁ ባይ ዘንድ መሔድ ኢስላማዊ ብያኔው ምንድነው?**
- ይህ ተግባር ክልክል ነው፡፡ እነሱ የሩቅ ዕውቀት አለን በሚሉት ሳያምን እራሱን ለመጥቀም ብሎ ወደነሱ የሄደ ሰው ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለሁ ባይ ዘንድ የሄደና የሆነ ነገር የጠየቀው ሰው የአርባ ቀን ሶላቱ ተቀባይነት የለውም) ብለዋል፡፡ ወደ እነሱ ሂዶ እነሱ ገይብን /የተሰወሩ ነገሮችን እናውቃለን የሩቅ እውቀቱ አለን የሚሉትን ያመነና የተቀበለ ሰው ደግሞ በነቢዩ ሙሐመድ ዲን/ሃይማኖት የካደ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ (ወደ ጠንቋይ ወይም አውቃለህ ባይ ዘንድ የሄደና የሚለውን ያመነው በሙሐመድ ላይ በተወረደው ቁርአን ክዷል) ብለዋል፡፡

- **በኢስላም ስለት መሳል እንዴት ይታያል?**
- ስለት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ) ስለከለከሉና እሱ ምንም ፋይዳ የለውም ስላሉ ስለቱ ለአላህ እንኳን ቢሆን መሳሉ ተገቢ ከናካቴው ስለቱ የተከለከለ ነው። የተገባውን ቃልም መሙላት አይፈቀድም። ስለዚህ ስለት በኢስላም ተቀባይነት የሌለውና ዋጋ ቢስ ድርጊት ነው።

- ዝናብን በኮከብ መለመን እንደ ማጋራት የሚቆጠረው መቼ ነው?
- ከአላህ ፍቃድ ውጭ ኮከቦች ዝናብን የማምጣት አቅም አላቸው ብሎ ያመነና ዝናብን የማዝነብን ስልጣን ለኮከቦች የሰጠ ሰው ትልቅ የሽርክ ተግባር የፈፀመ ነው፡፡ ኮከቦች በአላህ ፍቃድ ላይ ተፅዕኖ አላቸው ወይም ስልጣኑን ለመጋራት አቅም አላቸው ብሎ ያመነ ሰው፤ አላህ ለዝናብ መምጣት ምክኒያት አድርጓል ብሎ ያመነና አላህ የዝናብ መምጫን ምልክት ይህ ኮከብ ሲመጣ አድርጎታል ብሎ ያመነ ሰው በተጨባጭም ሆነ ከሸሪዐ እንዲሁም ከትክክለኛ አዕምሮ መረጃ ያለው አባባል ባለ መሆኑ ክልክልና ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ ነው፡፡ አመትን በወራቶች በመከፋፈል በኮከቦች ለያይቶ ማወቅና የዝናቡን መምጫ ወቅት በእሱ ለመረዳት መሞከር በኢስላም ምንም ችግር የለበትም፡፡